# ኤ ፒ (AP) አጠቃላይ መረጃ 2018

በቲ ሲ ዊሊያም ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ከምን ጊዜም የበለጠ የየከፍተኛ ምደባ ፕሮግራም (Advanced Placement) ኤ ፒ (AP) ከፍተኛ ነጥብ ያመጡ ተማሪዎች ቁጥር ከፍተኛ ነው።

የኤ ፒ (AP) ፈተና ከወሰዱ ተማሪዎች መካከል 22 ፐርሰንት የሚሆኑት የደረጃ አምስት ማለትም በ ኤ ፒ (AP) ፈተና ሊገኝ የሚችለውን ከፍተኛ ነጥብ አግኝተዋል። በተጨማሪም በ 2018 ዓ.ም መካከል የ72 ፐርሰንት ከተማሪዋቹ ሦስት፣ አራት እና አምስት ደረጃ አግኝተዋል - በኮሌጅ ቦርድ የሚፈለገው ነጥብ የኮሌጅ ነጥብ ለማግኘት የሚያስችለውን።

እኒዚህ ሁሉት ነጥቦች ከ2005 የትምህርት ቤት አስተዳደሩ ገንዘብ በመክፈል ተማሪዎች ፈተና እንዲወስዱ ከጀመረ ወዲህ ኤ ሲ ፒ ኤስ ታሪክ ከፍተኛው ውጤት ናቸው። በ 2005 ዓ.ም 5 ነጥብ ያገኙ ተማሪዎች ቁጥር 9 ፐርሰንት ነበር እና 39 ፐርሰንት ተማሪዎች ያገኙት ውጤት ሦስት እና ከዚያ በላይ ነበር። ከ2005 ዓ.ም ወዲህ በ ቲ ሲ ዊሊያም በአንድ ዓመት ጊዜ የታየ ከፍተኛ ጭማሪ ይህ ነው።

ከዚህ ከፍተኛ ነጥብ በተጨማሪ ብዙ ተማሪዎች በዚህ ዓመት የኤ ፒ (AP) ፈተና በዚህ ዓመት ወስደዋል። ከሦስት እጅ በላይ የሆኑት ተማሪዎች (36 ፐርሰንት) ከ10 እስከ 12ኛ ክፍል ያሉ ቢያንስ በ2018 አንድ የኤ ፒ (AP) ፈተና ወስደዋል - ይህም በትምህርት ቤት አስተዳደሩ 931 ተማሪዎች 2,021 የትምህርት ፈተና ዓይነቶችን በመውሰድ እስከ አሁን ካሉት ከፍተኛውን ቁጥር ይዘዋል።

ይህም በሁሉም መንገድ ከፍተኛ ውጤት ነው። በዚህ ዓመት ብዙ ተማሪዎች የኤ ፒ (AP) ፈተና መውሰዳቸው ብቻ አይደለም ከቀድሞ በበለጠ ውጤትም አግኝተዋል። "ኤ ሲ ፒ ኤስ ተማሪዎችን ጥሩ ውጤት እንዲያገኙ ድጋፍ ያደርጋል እና በሌላ ስፍራ የማይገኝ እድል እንዲያገኙም ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል።" ብለዋል Peter Balas የቲ ሲ ዊሊያም ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ርእስ መምህር።

የከፍተኛ ምደባ ፕሮግራም (Advanced Placement) የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች በኮሌጅ ደረጃ ያሉ ኮርሶችን እንዲወስዱ በማበረታታት እገዛ ያደርጋል። በፕሮግራሙ የሚሳተፉ ተማሪዎች በኮሌጅ ደረጃ ያሉ እውቅቶችን ብቻ አይደልም የሚያገኙት ነተጨማሪ ብዙውን ጊዜ በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እያሉ የኮሌጅ ክሬዲት ያገኛሉ።

ሁሉም የኤ ሲ ፒ ኤስ ተማሪዎች ኮርሱን የሚወስዱ ፈተና መውሰድ ይኖርባቸዋል። ይኽም ማለት ኮርስ መርጦ የጀመረ ትምህርቱን እጠናቆ የመመዘኛ ፈተናውንም መውሰድ ይኖርበታል። በ2005 ም የኤ ሲ ፒ ኤስ ባወጠው ፖሊሲ ኤ ፒ (AP) ኮርስ ያለክፍያ እንዲወስዱ ተደርጎል።

## ለሁለት ተማሪዋቻችን የ ኤ ፒ (AP) ክፍል የመውሰድ እድል ማግኘት ምን ማለት እንደሆነ እንደሚከተለው ቀርቦል፤



**ኤይዳን ዶኔላን (Aidan Donnellan)**
**ቲ.ሲ ዊሊያም ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት**

ኤይዳን ዶክተር የመሆን ፍላጎትን ሁሌ ያስባል። በጊዜ ቆይታ በ ቲ ሲ.ዊሊያም ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ባገኘው ልምድ ፍላጎት እየጨመረ ሲሆን እና ኑሮሣሳይንስ(neuroscience) እና ኬምስትሪ ወደ ማጥናት አዘንብሎል። እዚያ ላይ ለመድረስ ወደ ግቡ ለመድረስ እንዲችል የኤ ፒ (AP) ክፍል መውሰድን ጨምሮ ያገኘውን እድል በሙሉ መጠቀም እንዳለበት ያውቃል።

በ2019 በሚመረቅበት ወቅት ኤይዳን በሒሳብ፣ እንግሊዘኛ ፣ ታሪክ፣ በገቨርንሜንት፣ ሣይኮሌጂ፣ ኮምፒውተር ሣይንስ፣ እና ሌሎችም ኮርሶች ይወስዳል። የመጀመሪያ የኤ ፒ (AP) ኮርስ የወሰደው የአስረኛ ክፍል እያለ ነበር ።

"የ ኤ ፒ (AP) ኮርስ የወሰድኩት ብዙ ጥረት የሚጠይቅ ኮርሶችን ለመውሰድ ስለምፈልግ ነው። እንዲሁም የዚህ ዓይነት መሰል ስሜት ካላቸው ተማሪዋች ጋር መዋል ስለፈለኩ ነው። እኔ ባለኝ ልምድ መሰረት የኤ ፒ (AP) ኮርስ የሚያስተምሩ ያላቸውን በጣም የጠለቀ እውቀት ለማጋራት የሚችሉ ናቸው ስለሚያስተምሩት ትምህርት ከመደበኛ ክፍል በበለጠ " ይላል ኤዲያን።

የኤ ፒ (AP) ኮርስ መውሰድ በኮሌጅ ደረጃ የሚሰጥ ኮርሶችን በአካዳሚ በማዘጋጀት ላይ ብቻ የሚወሰን አይደለም። የኤ ፒ (AP) ኮርስ መውሰዱ ከክፍል ውጭ ባለው ህይወት ዝግጁ እና ተሳታፊ እንዲሆን አስችሎታል። የበጋ ጊዜውን በብሔራዊ የጤና ኢኒስቲቲዩት (NIH) የLupus team የክሊኒክ ሙከራ ምርምር ከሚሰራው ቡድን ጋር በመስራት አሳልፎል። ኤይደን ይህን እድል ያገኘው ባለፈው ዓመት እህቱ ከ NIH የመጣ ተጋባዝ ተናጋሪ በሚኒ ሐዋርድ በተካሄደው የስራ ቀን ያደረገው ገለፃ ያገኘችውን መረጃ ለእሱ ስላካፈላችው ነበር። በሲኒየር የመመረቂያ ዓመቱ የኤ ፒ (AP) ኮርስ ጫና ቀንሶታል ምክንያቱም በNIH የሚሰራውን ስራ ትምህርት በተጀመረበት የፎል ወቅትም አብሮ ለማስኬድ እንዲችል። .

“የ ኤ ፒ (AP) ኮርሶችን መውሰድ ለኮሌጅ እና በሕይወት ዘመን ተፈላጊ የሆኑ አስፈላጊ ክህሎት ችሎታዋችን ማለትም የስራ ስነስርዓት ፣ የጊዜ አጠቃቀምን ፣ አጠቃላይ ወሳኝ የአስተሳሰብ ዘዴን በማዳበር አሰራር ለማሳደግ እና ለማግኘት እገዛ አድርጎል። በተጨማሪም ከአስተማሪዎች ጋር በመግባባት በመገናኘት እና እርዳታ ሲያስፈልገኝ ለመጠየቅ የሚያስፈራኝ ስሜት አሁን የለም።”



ጃስሊን ፖዛ (**Jasselene Paz)**
ቲ.ሲ ዊሊያም ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

ጃስሊን ፖዛ ስለ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ልምዶ ስታወራ በደስታ አብዛኛው ነገር ከአስተማሪዋቻ ጋር ታያይዘዋለች።

“የእኔ ኮርሶዋች በትክክል በቲ ሲ ዊሊያም የነበረኝ የትምህርት ቆይታ ልምድ አስተዋፅኦ አላቸው። ከሆነር እና መደበኛ ክፍል ብዙ ነገር መማር የሚቻል ቢሆንም የ ኤ ፒ (AP) ትምህርት የሚሰጠው ለየት ባለ መልኩ ነው። እንደተማሪዋች ለእኛ በጣም አስፈላጊ የሆነ ትምህርት ነው የሚሰጠን እና እኛም እንደ ፈጣሪ እና የአዲስ እውቀት ተማሪዋች እንድንሆን ግፊት ይደረግብናል።” እኛ አብረን የምንሆነው ከሌሎች ተማሪዋች ጋር አንድ የትምህርት ርእስን በተለየ መንገድ ለመመልከት ከሚፈልጉ ጋር ነው። ለእኔ በጣም አስፈላጊ የሆነ ብዙ ነገር እየተማርኩ መሆኑን እናም አስተማሪዎቼም ለተማሪዋቻቸው ለማገዝ ከፍተኛ ፍላጎት አላቸው። ትምህርቱን በሚገባ እንደንከታተል ይገፉናል። እናም ተማሪዋች የኤ ፒ (AP) ፈተና እንዲወስዱ ኤ ሲ ፔ ኤስ ክፍያ መክፈሉ ተማሪዋች በገንዘብ ማነስ ምክንያት የሚወስዱትን የኤ ፒ (AP) ፈተና መጠን እንዳይወስኑ ያደርጋል። እስከምንችለው ድረስ የተለያየ የኤ ፒ (AP) ክፍል እንድንወስድ እድል ተሰጥቶናል።” ትላላች ጃስሊን።

በ2019 መጨረሻ ዓመት ስትመረቅ ጃስሊን 14 የኤ ፒ (AP) ኮርሶችን ትወስዳለች። በዚህ ፎል ወቅት ለማህበረሰቡ የመልሶ አገልግሎት በአርላንድርያ (Arlandria) ከመደበኛ ትምህርት በኋላ ለCasa Chirilagua ተማሪዋች ትምህርት የምትሰጥ ሲሆን ይህም በተለይ ችግር ሊያጋጥማቸው የሚችሉ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ያሉትን ልጆችን የማገዝ ስራ ወደፊት ለመስራት ላላት ዓላማ ዝግጅት ይጠቅማታል።